# የታለ ያ ጨዋነት!!

መይሳው ከምድረ ስዊድን

2011-12-17

አበው ያስተማሩን፤ አጥብቀው የመከሩን

ያለንን አካፍለን፤ አብሮ የመኖርን

አንዱ አንዱን አክብሮ፤ ችሎ ተቻችሎ

በፍቅር ተሳስሮ፤ በጥልቅ አስተውሎ

ወገኑን ረድቶ፤ የተጎዳ አቅንቶ

ለታረዘ አልብሶ፤ ለጠማው አጠትቶ

ለታመመው አስታሞ፤ እንባውን ረጭቶ

ቁም ስቃዩን አይቶ፤ ላምላኩ ቃል ገብቶ

ካንተ ያስቀድመኝ፤ ብሎ ተመኝቶ

ፀሎቱን ፀልዮ፤ አምላኩን ወትውቶ

ፈውስ ያገኘ ከሆነ፤ ስለት አስገብቶ

በረከት አውርዶ፤ ልቦናውን ከፍቶ

ጠላት ሲመጣበት፤ በ አንድ ላይ መክቶ

ምድር ቀውጢ ሆና፤ መግቢያ አሳጥቶ

እንደድር አብሮ፤ በሕብረት ተስማምቶ

ይሸኘው ነበረ፤ ድባቅ አስገብቶ

በችግር በደስታ፤ ሁሉ ተጠራርቶ

አንደኛው ለሌላው፤ ደግ ተመኝቶ

ነበረ የኖረው፤  ሁሉ አብሮ በልቶ::

ወይ ዘመን ወይ ጊዜ ? መተሳሰብ ጠፍቶ

በክፋት በተንኮል፤ ፍቅሩ ተተክቶ

ተጣመን ስናስብ፤ አጣመን እያየን

ደንካራ እየሆንን፤ ሚስጥር የማይገባን

በራሳችን ሚዛን፤ ሰፍረን እየለካን

ፍቅር መተሳሰብ፤ እንዲርቅ አድርገን

ይኸው እንኖራለን፤ እንዲህ እየፋደድን::

መከት ተነስ፤ አብር በጠላት ወያኔ

አደራ እንዳንበላ፤ ተመከር ወገኔ

አሁን መውደር ነው፤ መመንገል ከስሩ

ሕፃናት አዋቂ፤ እንዲያ እያስመረሩ

ፍትህ ጠያቂውን ፣ ጠፍረው እያሰሩ

ላገሬው ሳይበጁ፤ ለውጭ ፣ ያደሩ:

ደማ አለ በጃቸው፣ ከሕዝቡ የፈሰሰ

ሕፃናት አዋቂ፣ እንባ ያሳበሰ::

ወንካራ መሆኑን ከጎን ተውና፤ የ አበውን አጥብቅ

መሰረቱ እሱ ነው፤ የላላው እንዲጠብቅ::

መይሳው ከምድረ ስዊድን 2011-12-17